ማለት በምንም አይነት ምክንያት በሽተኛ በገዛ ራሱ ፈቃድ መድኀኒቶቹን ከመውሰድ ማቋረጥ አይገባውም። የመድሃኒቶቹ አወሳሰድና ብዛት በሃኪሙ የተሰጠውን መመርያ ሙሉ በሙሉ መተግበር ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን የሚወሰዱት መድኃኒቶች አላማቸውን መምታት አይችሉም።
በሽተኞች የሚሰጠውን ሕክምና እንዲጠቀሙ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ማድረግ አለባቸው።

- መድኃኒቶቹን ያለማቋረጥ በቀጣይ መውሰድ
- በየጊዜው የሕክምና ምርመራ ማድረግ
- በደም ውስጥ የሚገኙትን የቫይረሱንና የረዳት ሴሎችን ብዛት ማስመርመር።

ሐኪሞች ይሁኑ አብረዋቸው የሚሰሩት ሰራተኞች በሙሉ፤ የበሽተኛውን ምሥጢር ለመጠበቅ ቃል ገብተዋል። ሓኪሞች የበሽኛ ረዳት እንደ መሆናቸው መጠን፤ በሽተኞች እነሱን አምኖ ከበሽታቸው ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሁሉ፣ መወያየትና መጠየቅ ይገባቸዋል።
ማንኛውም የጀርመን ነዋሪ የጤና ዋስትና (ኢንሹራስ) አለው። ለሚደረግለት የህክምና አገልግሎት የሚከፍልለት የጤና ዋስትናው (ኢንሹራንሱ) ነው። በመንግስት እርዳታ የሚተዳደር ሰው ከሆነም፣ መንግስት ለጤና ዋስትናው ይከፍልለታል።
ጥገኝነት ለጠየቁ ሰዎች ደግሞ እነሱን የሚመለከት ልዩ ደንብ ስላለ፣ ምክር ሰጭዎች ዘንድ ሄደው ስለ ሕክምናቸው አከፋፈል ጉዳይ መነጋገር አለባቸዋል።

## ኤይድስ እና የመኖሪያ ፈቃድ፣

አንድ ሰው በትውልድ ሃገሩ የኤችአይቪ ሕክምና ለማግኘት የማይችል ቢሆንና ይህ ሰው ደግሞ ጀርመን ሃገር ውስጥ የኤችአይቪ ሕክምና ጀምሮ ከተገኘ፣ ወደ አገሩ እንዲመለስ ላይገደድ ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ በትውልድ አገሩ ሕክምና ለመቀጠል እንደማይችል የሚገልጽ ማስረጃ ለማግኘት ብዙ ግዜ  አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

## ስለ ኤችኣይቪ/ኤይድስ መነጋገር

በርግጥ በኤችአይቪ መያዝ ህይወትን ይቀይራል። ይህን አዲስ ሁኔታ ተቀብለው በህይወትዎ አዲስ ደስታ እንዲያገኙ፣ ቤተሰብ፤ ዘመድና በቅርብዎ ያሉ ሰዎች ሊያግዝዎት ይችላሉ። ሆኖም በዚህ ጉዳይ አምነው ከማን ጋር በግልጽ ለመነጋገር እንደሚችሉና ከማንስ እርዳታ ለማግኘት እንደሚቻል  በደንብ ያስቡበት።
ይሄንን ጉዳይ ለማነጋገር የሚያምኑት ሰው ባጠገብዎ ካላገኙ ግን፣ በአካባቢዎ የምክር አገልግሎት ሊያገኙበት የሚችሉበትን መንገድ መጠየቅ የገባል።

## የኤድስ ምክር ኣገልግሎት

Projekt Afrikaherz
VIA - Verband für interkulturelle Arbeit
Frau Rosaline Mzbayo
Petersburger Str. 92
10243 Berlin
Tel.: 030/4224706
afrikaherz@via-in-berlin.de

IAAGI gGmbH - Initiative against AIDS & Global Infections
Sulzbacher Straße 2-4
65812 Bad Soden
info@iaagi.info

Gesundheitsberatung für afrikanische Familien in Frankfurt am Main, Stadtgesundheitsamt
Braubachstr. 18-22
60311 Frankfurt/M.
Tel.: 069/212-33813

Light of Africa NRW e.V
Postfach 29 12 05
47832 Krefeld
Tel: 0173/7067307
info@loa-nrw.org

african support, c/o AIDS-Beratung Mittelfranken
Rieterstraße 23
90419 Nürnberg
Tel: 0911 / 322500

**ኤችአይቪን የሚያክሙ ሐኪሞች በዩኒቨርሲቲዎች ክሊኒክ ይገኛሉ**
**በተለይ የኤችአይቪ ሕክምና የሚሰጡ ስምና አድራሻ ከምክር ሰጪ ጽህፈት ቤቶች ያገኛል።**

Netzwerk Afro-Leben + in Deutschland, c/o Deutsche AIDS-Hilfe
Postfach 610149
10921 Berlin
www.afroleben.de

## ይህን የጽሑፍ መግለጫ በሚመለከተው ኣድራሻ ማግኘት ይችላሉ።

© 2007 AIDS-AUFKLÄRUNG e.V.,
Große Seestraße 31, 60486 Frankfurt,
Telefon: 069-762933, Telefax: 069-761055,
Internet: www.aids-aufkaerung.de
e-mail: info@aids-aufklaerung.de
Spendenkonto:
Frankfurter Sparkasse Konto 652 652, BLZ 500 502 01

AIDS AUFKLÄRUNG

# INFORMATION ZU HIV / AIDS IN AMHARISCH

## ስለ ኤችአይቪ/ኤይድስ መግለጫ

በአሁኑ ግዜ በዓለማችን በጣም አደግኛና ወደ ሞት ከሚያደርሱ በሽታዎች ዋናው ኤይድስ ነው፡፡ ኤይድስ ሃይማኖት፣ ቀለም፣ ዘር ይሁን ጾታ ሳይለይ ሁሉንም እኩል አድርጎ የሚይዝ በሽታ ነው። በተለይ ደግሞ የዚህን በሽታ መኖር በሚጠራጠሩ፣ በሚክዱ እና አስፈላጊውን የመከላከያ እርምጃዎች በማይወስዱ አገሮች፣ ይህ በሽታ በፍጥነትና በብዛት በመስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡
በአገርዎ የሚገኙ የኤይድስ ሕሙማንና በኤችአይቪ የተያዙ የሰዎች ቁጥር ብዛት፣ ከጀርመን አገር ካሉት በሽተኞች ጋር ሲወዳደር ከፍ ያለ ነው። የተባበሩት መንግስታት የጤና ድርጅት ሪፖርት እንደሚገልጸው፡ በዓለማችን ካሉት 40 ሚሊዮን በኤችኣይቪ ከተያዙ ስዎች ውስጥ፡ 28 ሚሊዮኑ ወይም ሁለት ሶስተኛው (2/3) ከሳሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሃገሮች ይገኛሉ።

## ኤችአይቪ ምንድ ነው?

ኤችአይቪ እጅግ ረቂቅ በአይን የማይታይ ተህዋስ (ቫይረስ) ነው። ይህ (ቫይረስ) የሰው ልጅ ሰውነት ውስጥ ገብቶ፤ የተፈጥሮ የህመም ተከላካይ የሆኑትን ሴሎች ያጠቃል፡፡

In Zusammenarbeit mit

Initiative against Aids & Global Infections
IAAGI
gemeinnützige GmbH

## ኤይድስ ምንድ ነው?

ነጭ የደም ሴሎች አካልን ከሁሉም አይነት በሽታ የሚከላከሉ ናቸው። ኤችአይቪ ሰውነት ውስጥ ገብቶ እነዚህን በሽታ ተከላካይ ሴሎች ስለሚያጠቃ፡ የነዚህ ሴሎች በኤችአይቪ መጠቃት ደግሞ ስውነታችን በሽታ የመከላከል ችሎታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደከመ ይመጣል። ከጊዜ ቡኋላም ሰውነታችን በሽታ የመከላከል ችሎታው ሙሉ በሙሉ ተንዶ ለተለያዩ በሽታዎች የሚጋልጥበት ሁኔታ ይደርሳል፤ ይህ የመጨረሻው ደረጃ ኤይድስ ተብሎ ይጠራል። ኤይድስ የሰው ልጅን በእርግጥ የሚገድል እስካሁን መድሃኒት ይሁን ክትባት ያልተገኘለት በሽታ ነው።

ኤችአይቪ ሰውነት ውስጥ ገብቶ፡ የሰውን ልጅ የመከላከያ ስርዓት አናግቶ የኤድስ ደረጃ ለመድረስ የሚያስፈልገው ግዜ ከሰው ወደ ሰው ብቻ ሳይሆን የሚለያየው፡ ከሃገር ወደ ሃገርም ይለያያል። ለምሳሌ ጀርመን አገር ከ10 እስከ 12 ዓመታት ያህል ሲሆን በሌሎች አገሮች ደግሞ ከዛ ባነሰ ግዜ ሊሆን ይችላል ማለት ነው።።

## ኤችአይቪ የትኛው የሰውነታችን ክፍል ውስጥ ይገኛል?

በብዛት ኤችአይቪ የሚገኝበት፡ ሥፍራ በደም፣ በአባለዘር፣ በሴት ብልት ፈሳሽና በእናት ጡት ወተት ውስጥ ሲሆን ምራቅ፣ እንባ፣ ሽንትና ሌሎች የሰውነት ፈሳሾች ውስጥ እጅግ ጥቂት ቫይረስ ቢገኝም ሕመሙ ግን በነዚህ ሊተላለፍ አይችልም።

## ዋና የኤችአይቪ መተላለፊያ መንገዶች

- የግብረስጋ ግንኙነት፡ ዋናው የኤችአይቪ መተላለፊያ መንገድ ያለኮንዶምና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው።
- በተበከለ ደምና የሰውነት ክፍል (organ)፡ በተበከለ ደምና የደም ውጤቶች፤ በሚለገስ የሰውነት ክፍል (organ) እና በወንድ አባላዘር ሊተላለፍ ይችላል። ያልመከኑ ሌላ ሰው የተገለገለባቸው እንደ መርፌ፣ መቁረጫና መቀደጃ በመሳሰሉ መሳሪያዎች ኤችአይቪ ሊተላለፉ ይችላል።
- ከእናት ወደ ልጅ፡ በኤችአይቪ የተያዘች እናት፣ በእርግዝና ወቅት፣ በወሊድ ጊዜ እና በምታጠባበት ግዜ በሽታውን ወደ ሕጻኑ ልታስተላልፍ ትችላለች። ስለዚህ በእርግዝና ወቅት የኤችአይቪ መድሃኒት በመውሰድ እንዲሁም በኦፐሬሽን ወሊድ የመተላለፉን ዕድል በጣም መቀነስ ይቻላል። ሕጻን ከእናት ወተት ሊጋባበት ስለሚችል፣ በኤችአይቪ የተያዘች እናት ልታጠባ ፈጽሞ አይገባም።

## ኤችአይቪ የማይተላለፍበቸው መንገዶች

በዕለታዊ ኑሮ ማለትም ከአንድ ብርጭቆ በመጠጣት፣ በመተቃቀፍ፣ በመሳሳም፣ በዋና ቦታ፤ በመጸዳጃ ቦታ፣ ልብስ፣ አንሶላና የብርድ ልብስ አብሮ በመጠቀም፣ አብሮ በመብላት፣ በትንኝ ይሁን በሽተኞችን መንከባከብ በመሳሰሉት ሁኔታዎች በሽታው አይተላለፍም። ስለዚህ በኤችአይቪ የተያዘን ሰው ካልተጨበጠ ፍራቻ ተነስቶ ማግለልና ግንኙነታችንን ማቋረጥ ተገቢ አይደለም።

## ኤችአይቪን እንዴት መከላከል ይቻላል፡

አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ታቅቦ የማይኖር ከሆነ፤ በልቅ ወሲብ ሊመጣ የሚችለውን የኤይድስ በሽታ ለመከላከል፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በኮንዶም ብቻ መፈጸም ይኖርበታል።

ኮንዶም መጠቀም ማለት ራሳችንን እና በግብረ ሥጋ የምንገናኛቸውን ሰዎች ከዚህ ወደ ምት ከሚያደርስ በሽታ መከላከል ስለሆነ፡ ይህን ማድረግ ደግሞ ከፍተኛ ኃላፊነትን የመውሰድ ምልክት ማለት ነው። ሃይማኖታዊ ይሁን ሌላ ምክንያቶች ሳያጠራጥሩን ኮንዶም መጠቀም የግድ ይሆናል። ያለ ኮንዶም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊፈጽሙ የሚችሉት፡ በደም ምርመራ ከበሽታው ነጻ መሆናቸውን ያረጋገጡ ጥምዶች ብቻ ናቸው።

ኤችአይቪ ያለበት ሰው መጀመሪያ ቫይረሱ ሰውነቱ ውስጥ ከገባበት ቀን ጀምሮ ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል። እንደዚሁም የኤችአይቪ መድሃኒቶች እየወሰደ የሚገኝ ሰውም ቢሆን፡ ቫይረሱን ሊያስተላልፍ ይችላል። በዚህ በሽታ የታመሙ ሰዎች ወደ ሌላ እንዳያስተላልፉ ከፍተኛ ሃላፊነት ስለ አለባቸው፡ ይህን ሃላፊነት ሊያከብሩት ይገባል። እያወቁ በሽታውን ቢያስተላልፉ ግን፡ በሕግ ያስቀጣቸዋል።

## የኤችአይቪ ምርመራ፡

አንድ ሰው በኤችአይቪ መያዝ አለመያዙን በዓይን በማየት ብቻ ማወቅ በፍጹም አይቻልም። ቫይረሱ ሰውነታችን ውስጥ መኖር፡ በደም (ጸረ ተህዋስ) ምርመራ ብቻ ነው ልናውቅ የምንችለው። የሰው ልጅ ለሆነ በሽታ ወይም ወረርሽኝ በሚጋልጥበት ግዜ ሰውነቱ ወዲያውኑ ጸረ ተህዋስ በመስራት መከላከል ይጀምራል። ስለሆነም ኤችአይቪ ወደ ሰውነት ውስጥ ልክ እንደገባ፡ ሰውነት ደግሞ ይህንን ቫይረስ ለይቶ አውቆ፤ በትክክል ለሱ ጸረ ኤችአይቪ መስራት ይጀምራል። ሰው ሲመረመር ደግሞ ደሙ ውስጥ ጸረ ተህዋስ መገኘቱን ወይም አለመገኘቱን ነው የሚታወቀው። ቢሆንም ሰውነት የኤችአይቪን ጸረ ተህዋስ እስኪሰራ የሚያስፈልገው ግዜ ከሰው ወደ ሰው ይለያያል። የአንዳንድ ሰዎች ሰውነት ጸረ ኤችአይቪ ለመስራት ጥቂት ሳምንታት ብቻ ሲያስፈልገው የሌሎች ሰውነት ደግሞ እስከ ሶስት ወር ያህል ግዜ ያስፈልገዋል። ስለዚህ እርግጠኛ የሆነ የደም ምርመራ ውጤት ለማግኘት ከተፈለገ፡ ያለ ኮንዶም የግብረ ሥጋ ግንኙነት (ልቅ ወሲብ) ከፈጸምንበት ቀን ጀምሮ፡ ከሶስት ወር ቡኋላ ነው ምርመራው መደረግ ያለበት ማለት ነው።

ማንኛውም ሃኪም ዘንድ ይህን የተባለውን የጸረ ተህዋስ (ደም) ምርመራ ማድረግ ይቻላል ቢሆንም እራስዎ መክፈል ይኖርቦታል። በመንግስት የጤና ድርጅቶችም ማንነትዎን ሳያሳውቁ ሊመረመሩ ይችላሉ። አድራሻዎችን ከማንኛውም የምክር አገልግሎት ሰጪ ጽህፈት ቤቶች ያገኛሉ።

እኛም በወገናችን ፍራንክፈርት ከተማ ውስጥ፡ በክንሃይም Große Seestraße 31 በሚገኘው ጽህፈት ቤታችን ውስጥ ማንነትዎ በማይታወቅ አገባብ፡ በባለ ሞያዎችና ሃኪሞች የሚካሄድ ከምክር ጋር የተሸኘ የጸረ ተህዋስ (የደም) ምርመራ አገልግሎት እንሰጣለን። በ15 ደቂቃ ውስጥ ደግሞ የምርመራውን ውጤት ያገኛሉ።

## ለኤድስ በሽተኞች የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት

በአሁኑ ግዜ ከዚህ በሽታ የሚያድን መድኃኒት የለም። ቢሆንም በሽታውን በማከም የበሽተኛን ዕድሜ ለማራዘም የሚረዱ መድሃኒቶች አሉ። እነዚህ መድኃኒቶች በሐኪም ክትትልና ቁጥጥር ስር በተወሰነ መጠንና ግዜ የሚወሰዱ ሆነው በቫይረሱ የተያዘው ሰው ወደ ጽኑ የኤይድስ በሽታ እስኪደረስ ያለውን ግዜ እንዲራዘም ለማድረግ የሚያስችሉ መድኃኒቶች ናቸው። ይህ የተጠቀሰው የህክምና ስልት፡ የተለያዩ መድሃኒቶችን ለበሽተኛ መስጠት ሲሆን፡ እነዚህ በብዛትና በዓይነት የተለያዩ መወሰድ የሚገባቸው መድኃኒቶች ደግሞ ከፍተኛ የመጥፎ ጎን ሊኖራቸው ይችላል። ስለሆነም ሰውነት ውስጥ ከገቡ ቡኋላ በአካላት ተግባራት ጣልቃ ስለሚገቡ እንደ ማቅለሽለሽ፣ የራስ ምታትና ተቅማጥ የመሳሰሉትን የሰውነት አለመስማማት ሊያስከትሉ ይችላሉ። እንደዚህ የመሰሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥም፡ በሽተኛ ከሃኪሙ ጋር መነጋገር አለበት። ምክንያቱም ሐኪሙ ከበሽተኛው ጋር ተማክረው ሌላ መድኃኒት እንዲቀይሩለት ወይም ደግሞ የመድሃኒቱ አለመስማማት ያስከተለውን ችግሮች ሊቀነስ የሚቻልበትን መንገዶች አብረው ማግሰብ ስለአለባቸው።

እነዚህ መድኃኒቶች በትክክል መወሰድ ይገባቸዋል፡ ይህ